

## <u>“የኢትዮጵያ ሺዓመት”</u>

### <u>መጭውን አዲስ ዓመት ” ፳፻ ” ዓ.ም. (2000) ብለን እንቀበለው!</u>

ከሁሉ በማስቀደም፤ እንኳን ለኢትዮጵያችን **፪ኛው ሺዓመት** መጠናቀቂያ በሰላም አደረሰን፤ **፫ኛውን ሺዓመት** በሰላም አቆይቶን በደስታ እንድንቀበለው የአምላካችን መልካም ፈቃዱ ይሁንልን ።

ኢትዮጵያ በዓለማችን ላይ ከሚገኙት አገሮች ሁሉ በብዙ መልኩ የተለየች በመሆንዋ ብዙዎች ይደነቁባታል። የምትደነቅባቸውም መሠረታዊ ነገሮች አያሌ ናቸው። ስለዚህም ከብዙዎቹ በሦስቱ መሠረታዊ ነገሮች ላይ ይህ ጽሑፍ የተኩራል። እነርሱም በከፍተኛ ደረጃ የምንኮራባቸው የጽሑፍ ፊደላ ችን፤ አኀዛችንና የዘመን አቆጣጠራችን ናቸው።

እንደሚታወቀው የዛሬ ሰባት ዓመት ገደማ ፈረንጆቹ በዘመን አቆጣጠር ቀመራቸው **“የሺዓመት”** በዓላቸውን (በነሱ አጠራር **ሚሌኒየም** የሚሉትን) አክብረዋል። ኢትዮጵያችንም ከሁለት መቶ አርባ አምስት (**፪፻፵፭**) ቀናት በኋላ የዚያንኑ ዓይነት ዓውደ በዓል በከፍተኛ ስሜትና ድምቀት ለመቀበልና ለማክበር እየተዘጋጀች መሆኗ ይታወቃል። ይህንን ዓውደ በዓል በትውልድ ተርታችን አጋጣሚ የደረስንበት ኢትዮጵያዉያን ሁሉ በምስጋናና በፍስሐ ልንቀበለው ይገባናል። የዚህን ዓይነቱን **የሺዓመት** ክብረ በዓል በሕይወት ኖረው ለማየት የሚበቁት ከብዙኅን የሰው ዘሮች መካከል ጥቂቶቹ መሆናቸው ግልጽ ነው።

የብቸኛው የኢትዮጵያ “**ሺዓመት**” አቀባበልና አከባበር መሪሃ ግብር ወጥቶ በመንግሥትም፣ በግለሰቦችም ደረጃ ጉዳዩ አትኩሮት እያገኘና እየታሰበበት፣ እየተመከረበትም ሲመጣ ብዙውን ሰው እያደናገረ ያለው የሁለት ሺህ ዘመን በግዕዝ አኀዝ አጻጻፍ ትክክለኛ ፈሩን መያዝ ነበረበት፡፡

ይሁን እንጂ መጭውን **ሺዓመት** ለማክበር በተዘጋጁ አርማዎች ላይ በግዕዝ አኀዝ ዓመተ ምሕረቱን ከመጻፍ ይልቅ በአረብኛ አኀዝ ተጽፎ ስለሚታይና በአንዳንድ ታትመው በተሰራጩ የማስታወቂያ ፖስተሮችና ሌሎችም ጽሁፎች ላይ ሁለት ሺህ ዓ.ምን በግዕዝ አኀዝ ለማመልከት “ **፪፻፼** “ተጽፎ ሰለሚገኝ የመጭው “**ሺዓመት**” የግዕዝ አኀዙ አጻጻፍ የስህተት አቅጣጫ ይዞ ይታያል፡፡ ይልቁንም በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ቃሉ ይናገር መጽሔት “**ለኢትዮጵያ 2000 ዓመተ ምሕረት (ሚሌኒየም) የተዘጋጀ ልዩ ዕተም ቁጥር 1፣ 1999**” ውስጥ በአረብኛ አኀዝ እንጂ በራሳችን የግዕዝ አኀዝ አንድም ስፍራ ተጽፎ አይታይም፡፡ “**አባት የያዘውን ልጅ ይወርሳል፣ እጅ የያዘውን አፍ ይጎርሳል**” ነውና ብሒሉ በዚህ ትልቅ ማህበር ዙሪያ ባሉ አበቶች የጎዳዩ አሳሳቢነት አልታወቀምን? በተከታታይስ ለአዲሱ ዘመን የሚታተሙት አጀንዳዎች፣ ካሌንደሮችና ሌሎች ሰነዶች ይህንኑ ስህተት ይደግሙት ይሆን? ከሚል ስጋት፣ የውይይት መነሻ ሀሳብ ተሰንዝሮ ሊቃውንትና ምሁራን የየበኩላቸውን አስተያየት ሰጥተውበት በጊዜ እርምት እንዲደረግ ለማሳሰብ ይህ አጭር የጽሁፍ ማብራሪያ ቀርቧል፡፡

በለፉት ገዜያት አንዳንድ መጻሕፍትን በመመርመርና በየአጋጣሚው ብዙ ሰዎችን **በግዕዝ አኀዝ ሁለት ሺህ ዓመተ ምሕረትን እንዴት እንጻፍ?** ብሎ በመጠየቅ ሀሣብ ለማሰብሰብ ተሞክሮአል፡፡ የብዙ ሰዎች አመለካከት የተሳሳተ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ አብዛኛው ሰው ሁለት **ሺን** በግዕዝ አኀዝ ሲጻፍ “ **፪፻** “ **ወይም** “ **፪፻፼** “ ነው ብሎ ያምናል፡፡ ብዙዎችንም የግዕዝ አኀዝ አጻጻፍ ጭራሽኑ አደናግሯቸዋል፡፡ ይህ “ **፪፻** “ አኀዝ በአረብኛው አኀዝ 200 እንዲሁም በግዕዙ ሲተረጎም “**ክልዔቱ ምዕት**” ወይም በተቀራራቢው ትግርኛ ቋንቋ **ክልተ ምዕቲ** ነው እንጂ 2000 አይደለም፡፡

ይህን “ **፼** ” እልፍ የግዕዝ አኀዝ በፊደል ገበታ ላይ በልጅነታችን የተዋወቅነው ትልቁ ቁጥር ሲሆን በአረብኛ አኀዝ ሲተረጎም 10.000 ነው፡፡ ይህ “ **፪፼** “ (**ሁለት እልፍ**) የሚያመለክተው ደግሞ 2 ቁጥርንና 10.000 ሲሆን 2፣ 1 ቁጥርን ተክቶ በአማርኛ፣ **ሀያ ሺህ** (20.000) ተብሎ ይነበባል እንጂ 2.000 አይሆንም፡፡ በሌላ አነጋገር በ 2 ቁጥር ላይ አራት ዜሮ 0000 (የ ፻ እና ፻ ዜሮዎች ማለት ነው) ተጨምሮበት 20.000 ይሆናል ለማለት ነው፡፡

የወጣቱ ክፍል የግዕዝ አኀዝ አጻጻፍ እውቀት ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ የተደረገም ሙከራ አለ፡፡ የወጣቱ ክፍል የግዕዝ አኀዝ ዕውቀት በእጅጉ አሳሳቢና አስገረሚም ነው፡፡ ያልዘሩትን አያጭዱምና፣ ለወጣቱ ያላሳየነውን፣ ያላስተማርነውን ከየት አምጣ ልንለው እንችላለን? ያብዛኛው ወጣት መልስ የግዕዝን አኀዝ ችሎታ ከሞላ ጎደል ከ **፩** - **፲** የሚዘል አይደለም፡፡ ቀስ በቀስ የኢትዮጵያ የግሏ የሆኑት መልካም እሴቶች ሁሉ እየጠፉ በመሄድ ላይ ለመሆናቸው ይህ ሁኔታ አንድ ማረጋገጫ ነው፡፡

ይህ “ ፼ “ እልፍ የምንለው አኀዝ አሥር ሺህ መሆኑን ብዙ ሰዎች ስለማያውቁት የሚከተለውን ሠንጠረጅ በዋቢነት እንመልከት፡፡

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ፲፻ | አሥርቱ ምዕት | 1,000 | ፷፻ | ሰድሳ (ስሳ) ምዕት | 6,000 |
| ፳፻ | እሥራ ምዕት | 2,000 | ፸፻ | ሰብዐ ምዕት | 7,000 |
| ፴፻ | ሠላሳ ምዕት | 3,000 | ፹፻ | ሰማንያ ምዕት | 8,000 |
| ፵፻ | አርባ ምዕት | 4,000 | ፺፻ | ተስዓ ምዕት | 9,000 |
| ፶፻ | ሃምሳ ምእት | 5,000 | ፼ | እልፍ | 10,000 |

በግዕዝ አኀዞቹ አናትና ግርጌ ያለው መለያ ጭረት፤ በግዕዙ **“ትርአስ እና ትርጋጽ”** ይባላል፡፡ በእውነቱ የግዕዝ አኀዛችንን አሟልቶ ለመረዳትና እጥቅም ላይም እንዲውል ለማድረግ የቤተ ክህነትን ለቃውንትና፤ የሌሎችንም ምሁራን ያላሰለሰ ጥረትና ምርምር እንደሚጠይቅ አሌ የሚባል አየደለም፡፡

የሮማውያን አኀዝ የላቲን ፊደልን ፤ I, II, III, IV,…………X, L, M, ወዘተ የሚጠቀም ሲሆን 0 (ዜሮ) አኀዝ የለውም፡፡ ለዚህም ነው አዉሮጳውያን የራሳቸውን አኀዝ ትተዉ በተውሶ አረብኛ አኀዝ 0፤1፣2፤3፤……9 የሚጠቀሙት፡፡ የሮማውያን አኀዝ ዜሮ የሌለው ቢሆንም አኀዙ የራሱ የሆነ የሒሣብ ስሌት ቀመር (ሥልት) እንደአለውና አራቱንም የሒሣብ መደቦች መሥራት እንደሚቻል ይታወቃል፡፡ የግዕዝ አኀዛችንም እንደ ሮማዉያን አኀዝ 0 (ዜሮ፤ አልቦ ወይም ባዶ) አኀዝ ባይኖረውም ቀደምት ሊቃውንት አባቶቻችን ለሒሣብ ስሌት አይጠቀሙበትም ነበር ብሎ ለመደምደም የሚያስቸግር ነው፡፡ ምክንያቱም አዳም ሲፈጠር ዘመን ሲቆጠር ጀምሮ ሰዓታቱን፤ ዕለታቱን፤ ወራቱንና ዓመቱን ቆጥረው፤ ዐራቱን ወቅቶች፤ ክረምትና በጋን፤ መፀውንና ጸደይን ለይተው እንዲሁም ሌሎቹን ሀሣበ ፀሐይንና ሀሣበ ከዋክብትን፤ ወዘተ መዝግበዉ ያቆዩን ሂሣብ አስልተው፤ ማለትም ደምረውና ቀንሰው፤ አባዝተውና አካፍለው መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ምን ዓይነት ቀመር እነ **“አቡሻክር”** ይጠቀሙ እንደነበር አባቶች ለቃውንት ለትውልድ ግልጽ ቢያደርጉ መልካም ነው፡፡

በዚህ ነጥብ ላይ መሪጌታ ይትባረክ ገሠሠ መራ “ **ኪነ ጥበብና ሥነ ጥበብ - የአኀዝ መዝገበ ቁጥር - ከነባር እስከ ምርምር** “ በሚለውና በ፲፱፻፹፮ ዓ.ም. በጻፉት መጽሐፋቸው ገጽ 9 ላይ “ **ለመሆኑ በግዕዝ ቁጥር ሂሣብን ለመሥራት የሞከረ ሰው አለ ወይ? ከልተሞከረስ ለምን አልታሰበበትም? በግዕዝ ቁጥር ሂሣብ መሠራት አለበት የሚለውን አስተሳሰብ መሠረት በማድረግ በአዲስ አበባ ብሔራዊ ዩኒቨርሲቲና በሌላ ዓለም ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ የቆዩ ምሁራን ኢትዮጵያውያንን አነጋግሬ እንደተረዳሁት የግዕዝ ቁጥር ሂሣብ ሊሠራበት እንደማይችል ተረጋግጧል የሚል ከምሁር አፍ የማይጠበቅ ተስፋ አስቆራጭ መልስ ነው ያገኘሁት፡፡** “ በለው ጽፈዋል፡፡

መሪጌታ የትባረክ ፊደላችን ምሉዕ አይደለም፤ ሞክሼ ሆሄያት ያደናግራሉ፤ አኀዛችን ለሂሣብ ስሌት (እንደ ዘመኑ የሂሣብ ስሌት ማለታቸው ይመስላል) ምቹ አይደለም በሚሉ ወገኖች አመለካከት ቁጭት ተነሳስተው ሳይሆን አይቀርም፤ ከላይ በተጠቀሰው መጽሐፋቸው በግዕዝ አኀዛችን አራቱን የሂሣብ መደብ ስሌቶች ለመሥራት እንድንችል አኀዛችን የሚጎድለውን ዜሮን ወይም አልቦን (ባዶን) በ፻ አኀዝ ሰይመው፤ ሌሎችንም የሥሌት ሰርዓቶች ቀምረው፤ የሥነ ጥበብ ምርምራቸውን ያቀረቡልን፡፡ የመሪጌታ ሃሣብ ከምርምር ደረጃ አልፎ በተግባር ስለመተርጎሙ ጸሐፊው መረጃ አላገኘም፡፡ ሀሣባቸውንና ጥረታቸውን ግን ልናደንቅላቸው ይገባል፡፡

የሞክሼ ፊደላትን በተመለከተ “**የአማርኛን ፊደል ጠንቅቆ የመጻፍ ችግርና መፍትሔ**” በሚል ርእስ ዶክተር አምሳሉ አክሊሉ በሪፖርተር መጽሔት ቁጥር 6፤ ነሐሴ 1995 በጉዳዩ ላይ “ **የቋንቋዎች መርሐ ልሳን (አካዳሚ)** “ ዉሳኔን አብራርተው ገልጸውታል፡፡ ይዚህ ጽሑፍ ባተኮረበት የግዕዝ አኀዝ አጻጻፍና ይዘት ላይ አካዳሚው ምን አቋምና ውሳኔ እንደለው ለጊዜው መረጃ አልተገኘም፡፡

ይሁን እንጅ፤ መሪጌታ ይትባረክ እነደጻፉትና ጸሐፊው በተመለከታቸው ሌሎች ልዩ ልዩ መጻሕፍት ቁጥሮች በአኀዝ በመጻፍ ፈንታ በፊደል ተጽፈው ይገኛሉ፡፡ ለምሣሌ “ወዘንተ ባሕቱ ኢትርስዑ አኀዊነ እስመ ዕለት በሀበ እግዚአብሔር ከመ <u>ዐሥርቱ ምዕት</u> ዓመት፡፡ ወዐሥርቱ ምዕት ዓመት ከመ አሐቲ ዕለት ኢይኄነዲ እግዚአብሔር ቃለ ዘነበበ፡፡” ይላል ፪ኛ ጴጥሮስ ም. ፫ ቁ. ፰ ፡፡ ትርጉሙ በአማርኛ፤ እናንተ ግን ወዳጆች ሆይ በጌታ ዘንድ አንድ ቀን እንደ ሺህ ዓመት፡፡ ሺህ ዓመትም እንደ አንድ ቀን እንደሆነ ይህን አንድ ነገር አትርሱ፤ ማለቱ ነው፡፡ ( ከላይ ዐሥርቱ ምዕት የሚለው ሺህ መሆኑን የጤኗል)፡፡

ትንቢተ ዳንኤል ም. ፯ ቁ. ፲ ላይ ደግሞ “የእሳትም ፈሳሽ ከፊቱ ይፈልቅና ይወጣ ነበር፤ ሺህ ጊዜ ሺህ ያገለግሉት ነበር፤ እልፍ አእላፋትም በፊቱ ቆመዉ ነበር፤ ፍርድም ሆነ፤ መጻሕፍትም ተገለጡ” ይላል፡፡

ይህንኑ የትንቢተ ዳንኤልን ጥቅስ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ብንመለከተዉ፤ “ A stream of fire issued and came forth from before Him; a thousand thousands served Him, and ten thousand times ten thousand stood before Him; the court sat in judgment and the books were opened” ይላል፡፡ (THE BIBLE, Version set forth 1611, Revised 1881 -1885, 1901, 1952, American Bible Society, N.Y.)

ከላይ የግዕዝ አኀዝንና ፊደልን አደባልቆ መጻፍም የተለመደ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ዶክተር ጌታቸው ኃይሌ በ፲፱፻፺፫ ዓ.ም. ባሳተሙት “**የአባ ባሕርይ ድርሰቶች - ኦሮሞችን ከሚመለከቱ ሰነዶች ጋር** “ በሚለው መጽሐፋቸው አባሪ ፩ “ ከአለቃ ታየ ትልቁ መጽሐፍ የተቀዳ” በሚለው ገጽ ፩፻፩ ላይ “ይህም አፄ የስሐቅ በነገሡ በ፭ ዓመት <u>በ፮ ሺህ ፱፻፩ዓመተ ዓለም፤</u> በ፲፩፻፩ ዓመተ ምሕረት ነው የሚሉ አሉ” ይላል፡፡ ቀደም ሲል በአኀዝ ሺህ ለመጻፍ ፲ አኀዝን ጽፈን ፻ አኀዝን በማስከተል እንደዚህ ፲፻ - ሺህ ይሆናል ብለናል፡፡ ከላይ እንደሚታየው (የተሠመተባቸውን ይመልከቱ) አኀዝ ዓይነት ከሺህ በላይ ያለውን ለመጻፍ፤ ማለትም፤ ከ፩ - ፱ ያሉትን አኀዞች አስቀድሞ፤ በሺህ ፊደል በማስከተል የሚቀጥሉት አኀዞች ይጻፋሉ፡፡ ሺህ ማለት ይህ ፲፻ ነው ብንልም የግዕዝ አኀዝ አጻጻፍ ሕግጋቱ ተለዋወጭ ስለሆነ አንድ ፈር ይዞ ስለማይሄድ ሊደበላለቅና ስህተት ሊከሰት ይችላል፡፡ ስለዚህ አንዳንድ ጊዜ አኀዝንና ፊደልን አደባልቆ መጻፍ ግዴታ የሚሆንበት ለዚህ ነው፡፡ ስለዚህ ሕግጋቱን በሰፊው ለመረዳት የቤተክህነትን ሊቃውንትና ተመራማሪ ምሑራንን ሃሣብ ማግኘቱ ጠቃሚ ነው፡፡

ይሁን እንጂ፤ አብዛኛውን ሰው ግራ የሚያጋባው እልፍ የሚባለው ይህ “ ፼ “ አኀዝ ሲሆን፤ ብዙ ሰዉ አንድ ሺህ ነው ብሎ ያምናል፡፡ የተጣመሩት የመቶና መቶ ምልክቶች ሲባዙ አሥር ሺህ እንደሚሆኑ ከዚህ በላይ ባመለከትሁት ሠነጠረጅ ላይ አመልክቼአለሁ፡፡ ከዚያ የሚያልፍም የግዕዝ አኀዝ ያለ የማይመስላቸው ሰዎች አይታጡም፡፡ ከላይ በትንቢተ ዳንኤል የተመለከተው ጥቅስ ሺህ ጊዜ ሺህ የሚለው በፊደል ይጻፍ እንጅ አንድ ሚሊዮን መሆኑን ያመለክታል፡፡ ከዚህም በላይ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ከ “ ፼ “ በላይ ያለዉን ሥርዐት ጽፈውታል፡፡ መምህር ፍስሓ ጽዮን ካሣ የተባሉም ጸሐፊ በ፲፱፻፹፫ ዓ.ም መጽሐፋቸው በገጽ ፸፫ የአኀዝ ቁጥሮችን ቀልለው ያሳያሉ፡፡ እነዚህ ሊቃውንት በአቀራረባቸው የሚመሳሰሉበትም

የሚራራቁበትም ባሕሪያት አላቸው። ነገር ግን የግዕዝ አኀዞቹን ከአረብኛ አኀዞች ጋር ተርጉሞ የአዲሱ ትውልድ እንዲረዳው ማድረግ ጠቃሚ ነው።

ስለሆነም፤ የግዕዝ አኀዛችንን ሥርዓት ለይቶ የማያውቀዉ እንዲረዳው ያህል እስቲ በምሳሌነት የሚቀጥለውን ሰንጠረዥ እንመልከት፤

| አኀዝ | ግዕዝ | አማርኛ | በአረብኛ አኀዝ |
|---|---|---|---|
| ፲ | አሥርቱ | አሥር | 10 |
| ፻ | ምዕት | መቶ | 100 |
| ፲፻ | አሥርቱ ምዕት | አንድ ሺህ | 1000 |
| **፳፻** | **እሥራ ምዕት** | **ሁለት ሺህ** | **2000** |
| ፼ | እልፍ | አሥር ሺህ | 10.000 |
| ፲፼ | አእላፍ | መቶ ሺህ | 100.000 |
| ፻፼ | አእላፋት (ምዕት እልፍ) | ሚሊዮን | 1.000.000 |
| ፲፻፼ | ትእላፍ | አሥር ሚሊዮን | 10.000.000 |
| ፼፼ | ትእልፊት | መቶ ሚሊዮን | 100.000.000 |
| ፲፼፼ | ትእላፋት | ቢሊዮን | 1.000.000.000 |
| ፻፼፼ | ምእላፍ | አሥር ቢሊዮን | 10.000.000.000 |
| ፲፻፼፼ | ምእልፊት | መቶ ቢሊዮን | 100.000.000.000 |

ከዚህም በተጨማሪ ጥንታውያን የብራና ግዕዝ መጻሕፍት፤ የአኀዞቹን ተራ ከላይ የተገለጹትን ጨምሮ እልፍ፤ አእላፍ፤ አእላፋት፤ ትእላፍ፤ ትእልፊት፤ ትእላፋት፤ ምእላፍ፤ ምእልፊት፤ ምእላፋት፤ አእላፈ አእላፋት፤ ትእልፊተ አእላፋት፤ ብለው ይደረድሩዋቸዋል።

የዚህ ጽሑፍ ጭብጥ በሚከተሉት ሁለት ዐበይት ጉዳዮች ላይ ያተኩራል። እነርሱም፤

፩ኛ፤ የመጭውን ዘመን አሠያየም የባዕድ ቃል **ሚሌኒየም** የሚለውን ከመውረስ ይልቅ ለምን ሁሉም ኢትዮጵያዊ እንዲዋጥለትና በትክክል እንዲረዳው ተስማሚ ወይም ተቀራራቢ በሆነ የአማርኛችን ቃል አንጠቀምም?

፪ኛ፤ **በግዕዝ አኀዝ ፲፱፻፺፱ ዓ.ም** ብለን ስንጽፍ እንደነበረው ቅርጹና ይዘቱ፤ እንዲሁም ሥርአቱ ሳይፋለስ መጨውን ዘመን በግዕዝ አኀዝ አስተካክለን በመጻፍ ለምን ለመጭው ትውልድ አናስተላልፍም? ናቸው።

በተራ ቁጥር ፩ ለተጠቀሰው **“ሺዓመት”** የሚለው ቃል **ሚሌኒየም** የሚለውን የእንግሊዘኛ ቃል በትክክል ይተካል፡፡ የባዕድ ቃላትን አደባልቆ መጠቀም ዘመናዊ አያደርግም፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳያጣ ያጣ መሆንም የለበትም፡፡ አባቶቻችን ምስጋና ይግባቸውና ለቋንቋችን ያማረ ፊደል ቀርጸዉ አቆይተውናል፡፡ ለመሆኑ ሚሌኒየም ምንድነው? ሚሌኒየም፤ በእንግሊዘኛው “Millennium” ከሁለት የላቲን ቃላት የተመሠረተ ቃል ነው፡፡ እነርሱም፤ “mille” ሲነበብ በአማርኛ **“ሚል”** ማለት ሺህ ሲሆን ፤ “annus” በአማርኛ ሲነበብ **“አነስ”**፤ ትርጉሙ **ዓመት** ማለት ነው፡፡ በላቲን “Annus mirabilis” በእንገሊዘኛው “Marvellous year” ሲሆን ወደ አማርኛ ሲመለስ **አስደናቂ ዓመት** ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ለሚሌኒየም የማያወላውል ተመሳሳዩ ቃል በአማርኛ እያለን ሚሌኒየም የሚለውን ቃል ፈረንጆች ስለተጠቀሙበት፤ አዙረን ሳናስተውል እንደወረደ መጠቀም አለብን?

መጭውን **ሺዓመት** በዘመኑ ያለነው ትውልድ ለመቀበል ተቃርበናል፤ እግዚአብሔር ሲፈቅድልን እናያለን፡፡ የወደፊቱን ሺዓመት መጭው ትውልድ ይቀበላል፤ ያያል፡፡ የወደፊቱም እንዲሁ እየተተካካ ያያል፡፡ አሁንም የቅርቡ አለ፤ ወደፊትም **ሺዓመት** (እስከዚያውም የዓለም ፍጻሜዋ ካልሆነ) ይመጣል፡፡ ስለዚህ በባዕድ ቋንቋ ከመጠቀም ይልቅ **ሚሌኒየም** የሚለውን በራሳችን ቃል **ሺዓመት** ብለን ብንተካውና በራሳችን አማርኛ ብንጠቀም ተገቢና ትክክለኛም ይሆናል ፡፡ ከዚህ የተሻለም ቃል አለ ከተባለ ተቀብለነው ልንጠቀምበት ይገባል፡፡ ለአንድ ቋንቋ የቃል ሥያሜ ለመስጠት የተናጋሪውንም ሆነ የአድማጩን ስምምነትና መግባባትን ነው የሚጠይቀው፡፡ ብዙኀኑ የአገራችን ሕዝቦች **ሚሌኒይም** የሚለዉን ቃል በትክክል ይረዱታልን? ብለን ማሰብም ይኖርብናል፡፡

**ሚሌኒየም** ለሚለው ቃል የኦሮሚፋ ትርጉም “ **በርኩሜ“ ነው፡፡** **በርኩሜ** ከሁለት ቃላት ጥምረት ወይ ቁርኝት የተገኘ ቃል ነዉ፡፡ በኦሮሚፋ “ **በረ** “ ማለት ዘመን ማለት ነው፡፡ “ **ኩማ** “ ማለት ደግሞ ሺህ ማለት ነው ፡፡ ስለዚህ፤ **በርኩሜ** ማለት በአጭሩ **“ሺዓመት”** ማለት ስለሆነ **ሚሌኒየም** የሚለው የባዕድ ቃል በኦሮሚፋ ቋንቋ በትክክል ተተርጉሟል፡፡ ኦሮሚፋ ተናጋሪውም ሕብረተሰብ በጥሩ ሁኔታ እንደተረዳው ገልጽ ነው፡፡

የብዙ አገር ቋንቋዎች የተለያዩ ቃላትን አቆረኝተዉ ወይም አጣምረው በአንድነት አንድ ቃል የመፍጠር ዘይቤ አላቸው፡፡ በተለይም የጀርመንኛ ቋንቋ ብዙ የሚዋዋጡና በቁርኝት የሚፈጠሩ በዙ ቃላቶች አሉት፡፡ እየተቆራኙ ቃላት የመፍጠር ሥርዓት ያላቸው ቋንቋዎች በእንግሊዘኛው ቋንቋ፤ “Agglutinative Languages” ይባላሉ፡፡ በጸሐፊው ትርጉም፤ **“ጥምር ወይም ቁርኙ ቃላት ያሏቸው ቋንቋዎች”** ማለት ነው፡፡ የኦሮሚፋው **በርኩሜ** የዚያን ዓይነቱን የቃላት ቁርኝት ስልት የተከተለ ነዉ፡፡

በኢትዮጵያችን ከውጭ ቋንቋ ከመዋስ ይልቅ በቅድሚያ በአገራችን የሉትን ቋንቋዎች ብንፈትሽ ለችግራችን መፍትሔ ይገኛል፡፡ ኢትዮጵያ የብዙ ብሔር ብሔረሰቦች አገር እንደመሆኗ መጠን ብዙ የተለያዩ ቋንቋዎች ይነገሩባታል፡፡ ከኦሮሚፋ፤ ከጋሞኛ፤ ከወላይተኛ፤ ከጉራግኛ፤ ከሽናሽኛ፤ ከአፋርኛ፤ ወዘተ ቋንቋዎች ለብዙ ከባዕድ ቋንቋ ለወረስናቸው ወይም ለምንወርሳቸው ቃላት ሁሉ (ምናልባት፤ አንዳንድ ቴክኒክ ነክ ከሆኑት በስተቀር) ለሕዝባችን የቀለለና ብዙ የልራቀ ቃል ለማግኘት የምንችል ይመስለኛል፡፡ ለምሳሌ፤ **“ጉዲፈቻ”** የሚለው የኦሮምኛ ቃል ጽኑ የባሕል መሠረት የአለው ነው፡፡ **ጉዲፈቻ**፤ በጽንሠ ሃሣቡና ባሕላዊ መሠረቱ ከመሰል የአማርኛ ቃላት የተሻለና ምሉዕ ሆኖ በመገኘቱ የአማርኛ ቋንቋ ተውሶት እየተጠቀምንበትና እየተግባባንበት እንገኛለን፡፡ **በሕገ መንግሥት**፤ ቀድሞም በነበረው፤ አሁንም ተሻሽሎ በሥራ ላይ በሚገኘው የ፲፱፻፺፪ ዓ.ም **የቤተሰብ ሕግ - ምዕራፍ ፲** ከአንቀጽ ፻፹ - ፻፺፮ የጉዲፈቻ ባህላዊ ሥርዓት ሕጋዊ መሠረትና አቋም አግኝቶ እየተሠራበት ይገኛል፡

ወደ ፪ኛዉ ነጥብ ስንመጣ፤ ከላይ በስጠረዡ ውስጥ እንደታየው የሁለት ሺህ ዘመንን በግዕዝ አኀዝ የምንጽፈው " ፳፻ " ብለን ነዉ። የዚሁ ዓመተ ምሕረት የመጀመሪያ ቀን፤ ቅዱስ ዮሐንስ፤ በዓለ ዓውደ ዓመት **መስከረም ፩ ቀን ፳፻ ዓ.ም.** ይውላል።

በግዕዙ አኀዝ ስልትም ሆነ በአምክንዮ ከላይ የተመለከተው የዓመተ ምህረት ዘመን አጻጻፍ ትክክለኛ ነው። ፈረንጆች ከሺ በላይ የለን ቁጥር ለምሣሌ፤ 1200ን፤ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ከማለት ይልቅ፤ አሥራ ሁለት መቶ (Twelve Hundred) ማለት ይቀናቸዋል። እንዲሁም 1500ን አሥራ አምስት መቶ (Fifteen Hundred) ይሉታል:: እኛ ኢትዮጵያውያንም ዘመንን ስንቆጥር የነበርነው፤ አሥራ ሰድስት መቶ፤ አሥራ ሰባት መቶ፤ አሥራ ስምንት መቶ፤ ብለን ነው። አሁንም ያለንበትን ዘመን **አሥራ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ዘጠኝ** እያልነው ነው። ይኸው ዘመን በግዕዝ አኀዝ ሲጻፍ ፲፱፻፺፱ (1999) ነው። መጭው ዘመን ደግሞ ፳፻ (2000) ተብሎ የጻፋል። ሲነበብ እንደተለመደው **ሀያ መቶ** ወይም ሁለት ሺህ ብለን ልንለው እንችላለን። የሀያ መጀመሪያዋ ቁጥር 2 እና 0 (ዜሮ) እንዲሁም ከመቶ ሁለት 0 (ዜሮ )ዎች ጋር አንድነት 2000 ይሆናል ማለት ነው። ከዛሬ አንድ ሺህ ዓመት በፊት የተከበረው ቅዱስ ዮሐንስ፤ በዓለ ዓውደ ዓመት **መስከረም ፩ ቀን፤ ፲፻ ዓ.ም.** ነበር። **፲፻ ( ሲነበብ አሥር መቶ)** ሺህ ነው። ከልደተ ክርስቶስ በኋላ የመጀመሪያው **ሺዓመት** የተፈጸመበት ዓ.ም. መሆኑ ነው። ከዚህ ቀንና ዓ.ም. ዘጠኝ መቶ ዓመት በኋላ የተከበረው ቅዱስ ዮሐንስ፤ በዓለ ዓውደ ዓመት **መስከረም ፩ ቀን፤ ፲፱፻ ዓ.ም. (ሺህ ዘጠኝ መቶ)** ነበር። ከዚያን ዘመን ጀምሮ አሁን በመገባደድ ያለው **ሺዓመት**፤ **፲፱፻፩ ዓ.ም**፤ **፲፱፻፪ ዓ.ም**፤.... **፲፱፻፳** ዓ.ም... ወዘተ እየተባለ ተቆጥሮ ነው እስከ **፲፱፻፺፱** ዓ.ም የተደረሰው። ስለዚህ መጭውን ዘመን " **፳፻ ዓ.ም.** " ብለን በመቀጠል ለመጭው ተረካቢ ትውልድ ትክክለኛውን አኀዝ ብናስተላልፍ ይበጃል ። ይሁን እንጂ፤ **፪** አኀዝን በሺህ ፍደልና ቁጥሩም ከፍ ሲል በሌላ ተጨማሪ አኀዝ አጅቦ፤ ማለት **፪ ሺህ** ዓ.ም ፤ **፪ ሺህ፩**፤ **፪ ሺህ፪**፤ ............ **፪ ሺህ፲**፤....... **፪ ሺህ ፶** ዓ.ም. ወዘተ እያሉ መጻፍም ስህተት አይሆንም። ምርጫው የእያንዳንዱ ሰው የግሉ ነው።

ውድ አንባብያን!

የዚች አጭር ጽሑፍ አቅራቢ የጋራና አንገብጋቢ ጉዳይ ላይ ሰፊ አመለካከትና የጠለቀ ዕውቀት ያላቸው አያሌ የቤተክህነት ሊቃውንትና ምሁራን፤ በአገር ውስጥም፤ በውጭ አገርም፤ እንዳሉ ይገነዘባል። ስለሆነም፤ ጽሑፉን የአነበቡ ሁሉ ሀሳባቸዉን ቢገልጹ፤ ሌላ አማራጭ ካለም ትክክሉ ይሄ ነው ብለው የሚሉትን ቢያሳውቁን በአገር ደረጃ በጉዳዩ ላይ አንድ አቋም እንዲያዝ እንደሚጠቅም ያምናል። እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ።

---

**ጸሐፊውን ፤ በሚቀጥለው አድራሻ ማግኘት ይቻላል፡ ኢዮቤድ ጥበቡ ልሣነወርቅ፤**
Eyobed Tibebu Lisanework; **Email Address: <eyobedtl@ethionet.et>**